የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

# የቴሌኮሙኒኬሽን መሠረተ ልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ ቁጥር 793/2013

**2013 ዓ.ም**

# የቴሌኮሚኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ

የኔትወርክ አቅምና ብቃት ፣ የሚሰራጩ የመቀበያ ጣቢያዎችን፣ ዋና መስመሮችን ፣ ማማዎች እና የኔትወርክ አገልግሎቶች ኢንቨስትመንት መደራረብ እና የኔትዎርክ ዝርጋታ ወጪን መቀነስን እና የኔትወርክ መሠረተልማት አጠቃቀምን ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ የደራሽነት አገልግሎት ስምምነት የሚዘጋጅበት እና የሚተዳደርበት አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ማበጀት አስፈላጊ መሆኑን በማንዘብ፤

የሃገሪቱ የሚልክዓ ምድር ገፅታ ጉዳት እንዳይደርስበት የማማዎች ተከላና መስፋፋትንም በመቀነስ አካባቢን ማጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የትብብር ከባቢ ሁኔታ በመፍጠር በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ወድድርን ማዳበር አስፈላጊ መሆኑ በመታመኑ፤ በኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(2) ፥ 44(5) ፥ 44(10) እና 54(2) መሰረት ባለስልጣኑ ይህንን የቴሌኮሚኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቴሌኮሚኒኬሽን መሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን መመሪያ ቁጥር 793/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜዎች

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ፤

1) **"የደራሽነት ስምምነት"** ማለት በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ወይም በቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት አቅራቢዎች ወይም በመሰረተ ልማት አቅራቢዎች መካከል የኮሎኬሽን ቦታ ወይም መሰረተ ልማት መጋራት አገልግሎትን የተመለከተ ስምምነት ነው።
2) **"የደራሽነት አቅራቢ"** ማለት የኮሎኬሽን ቦታ እና የመሰረተልማት መጋራት አገልግሎት ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም ለቴሌኮሚኒሽን አገልግሎት ሰጪ የሚሰጥ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ወይም የመሰረተ ልማት አቅራቢ ነው።
3) **"ደራሽነት ፈላጊ"** ማለት ከደራሽነት አቅራቢ ደራሽነት ለማግኘት የሚፈልግ ወይም የደራሽነት አገልግሎት ያገኘ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ነው።
4) **"የደራሽነት አገልግሎት"** ማለት አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ለሌላ ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ የሚሰጠው የኮሎኬሽን ቦታ እና/ወይም የመሰረተልማት መጋራት አገልግሎት ነው።

5) **"ገባሪ መሠረተ ልማት"** ማለት አንቴናዎችን፣ ሰዊቾችን፣ ሰርቨሮችን፣ የሚጃ ቋቶችን፣ የማከፋፈያ ወይም የሬዲዮ መዳረሻ ኖድ እና የማስተላለፊያ መሣሪያዎችን ጨምሮ በገባሪ የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ንብርብር ላይ ያሉ ክፍሎች ወይም አካላት ናቸው፤

6) **"ቋሚ መሠረተ ልማት"** ማለት የገባሪ ቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ መሠረተ ልማት ንብርብር አካል ያልሆነ መሠረተልማት ሲሆን የሥራ ቦታዎችን፣ ሕንፃዎችን፣ ማጠለያዎችን፣ ማማዎችን፣ ረዣዥም ቋሚዎችን፣ ምሰሶዎችን፣ ማስተኛ ጉድጓዶችን፣ ጠብብ ቦዮችን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እና የአየር ማቀዝቀዣን ጨምሮና ሌሎችንም የሚያካት ማስረተ ልማት ነው።

7) **"ባለሥልጣን"** ማለት በኮሚኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኮሚኒኬሽን ባለሥልጣን ነው፤

8) **"ኮሎኬሽን"** ማለት አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የሌላኛው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የኔትዎርክ መሳሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሠረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ ነው።

9) **"መሰረተልማት አቅራቢ"** ማለት ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች ወይም ለቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች መሰረተ ልማት የማጋራት ዓላማን በመያዝ ቋሚ መሰረተ ልማትን በባለቤትነት የመያዝ፥ የመገንባት፥ የማስተዳደር ወይም በሌላ መንገድ ለማቅየት ፍላጎት ያለው መሰረተልማት አቅራቢ ነው።

10) **"የመሠረተ ልማት ማጋራት"** ማለት በተዋዋዮቹ መካከል የሚደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የደራሽነት አገልግሎት አቅራቢ ከደራሽነት ጠያቂ ጋር ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ ልማቶችን የሚጋሩበት ሂደት ሲሆን የኔትወርክ ክፍሎችን፣ ሥርዓቶችን፣ መሣሪያዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ ቅጥር ግቢዎችን የመጠቀም መብቶችን ጨምሮ ሌሎችንም ያካትታል። ፤

11) **"የማገናኘት አገልግሎቶች"** ማለት የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ትስስራቸውን ለማስካት በማሰብ አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ለሌላው ኦፕሬተር የሚሰጠው አገልግሎት ነው፤

12) **"የመሰረተ ልማት ማጋራት አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ"** ማለት ለደራሽነት ስምምነት የተዘጋጀ መደበኛ ቅጽ ሲሆን በተለያዩ ክፍል የተከፈለ አግባብነት ያላቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ክፍያን ጨምሮ ተጓዳኝ ህጎችን እና ሁኔታዎችን የሚገልጽ ሰነድ ነው።

13) **"የቴሌኮሚኒኬሽን ችርቻሮ አገልግሎት"** ማለት ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ሳይሆን ለህዝብ በቀጥታ የሚቀርብ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ነው፡፡

14) **'የስራ ቀናት'** ማለት ስራ የሚሰራባቸው ቀናቶችን ብቻ የሚያካትት ሲሆን ቅዳሜ እሁድ፥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ባሕላት ተብለው የተለዩ ቀናቶችን አይጨምርም።

**3. ዓላማዎች**

የዚህ መመሪያ ዋነኛ ዓላማዎች፡ –

1) የደራሽነት ስምምነቶችን የሚያስተዳድር ሚቀፍ ማዘጋጀት፤

2) በአዋጁ አንቀጽ 44 መሠረት የመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽንን ለመቆጣጠር ባለሥልጣኑ ሊከተል የሚገባቸውን ደንቦች እና አሠራሮች ግልፅ እንዲሆኑ ማድረግ፤

3) የኔትወርክ ዝርጋታ ወጪን መቀነስ፤

4) የሀገሪቱ የሚልክዓ ምድር ገፅታ እንዳይለወጥ የማማዎች ተከላና መስፋፋትን በመቀነስ አካባቢን ማጠበቅ፤

5) የትብብር ከባቢን በመፍጠር በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ወድድርን ማዳበር፤

6) የኔትዎርክ አቅምና ብቃት ፣ የማስራጫ የመቀበያ ጣቢያዎችን፣ ዋና መስመሮችን ፣ ማማዎች እና የኔትዎርክ አገልግሎቶች ኢንቬስትመንት መድራረብ መቀነስን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን የኔትወርክ መሠረተልማት አጠቃቀምን ማስደግ፤

7) መሠረተ ልማትን ማጋራት የሚያስገኛቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ለአጠቃላዩ የቴሌኮሚኒኬሽን ባለድርሻ አካላት ጠቀሜታ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፤

8) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች በደንበኞች ላይ የሚጥል የክፍያ ተመን የመቀነስ ተጨማሪ ወጠት ያለው የወጪ ቅነሳ በማድረግ ብቃትን የማስደግ ፖሊሲ እንዲከተሉ ማበረታታት፤ እና

9) በመሠረተልማት ግንባታ እና/ወይም ዝርጋታ ከሚሳተፉ ሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጋር ባለሥልጣኑ እንዲቀናጅና እንዲተባበር ማስቻል፤

ናቸው፡፡

**4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚገኙ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች፥ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች እና የመሰረተ ልማት አቅራቢዎች ላይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የባለሥልጣኑ ሚና

**5. <u>የባለስልጣኑ ሚና</u>**

1) ባለሥልጣኑ

(ሀ) በቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች እንዲሁም በሌሎች ቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ ወስጥ የሚገኙ አግባብነት ያላቸው አካላት መካከል የደራሽነት አገልግሎት አቅርቦት ለማምቻቸት እና ለማበረታታት ጥረት ያደርጋል፤

(ለ) የደራሽነት አገልግሎቶችን ይቆጣጠራል፤

ሐ) በቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች እንዲሁም በቴሌኮሚኬሽን ዘርፍ ላይ በተሰማሩ አካላት መካከል የደራሽነት አገልግሎት አቅርቦቶች የሚሟሉባቸው ደንቦች በከፍተኛ ደረጃ ተአሚኒት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤

(መ) ተዋዋይ ወገኖች በደራሽነት አገልግሎቶች ድርድር ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ በአዋጁ አንቀጽ 44 (4) እና 44 (9) መሠረት የስምምነቱን የወል ቃሎች ለመወሰን ጣልቃ ይገባል፤ እና

(ሠ) አግባብ ካለው ፈቃድ ጋር ተጣጥሞ እንደሚሄድ ለሚረጋገጥ እና ወድድርን የሚጎዱ ስጋቶችን ለመቀነስ ባለስልጣኑ በሚኸቸውም ጊዜያት የመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን ስምምነቶችንን የመጠርመር መብት አለው፡፡

2) ባለሥልጣኑ፤

(ሀ) በራሱ ሥልጣን ወይም በደራሽነት ስምምነት ተዋዋይ ወገን ጥያቄ የመሠረተልማት ማጋራት እና የኮሎኬሽን ክፍያዎች ወጪ ማስረት ያደረጉ መሆን አለመሆናቸውን ይወስናል፤

(ለ) በራሱ ሥልጣን ወይም በተዋዋይ ወገን ጥያቄ በደራሽነት ስምምነት ላይ የሚነሳ አለመግባባትን በባለስልጣኑ አለመግባባት መፍቻ መመሪያ አንቀጽ 22 መሰረት ይፈታል፤

(ሐ) ለቴሌኮሚኬሽን አገልግሎቶች አቅርቦት ሲባል የሚከናወን የመሰረተ ልማት ዕቅድን፣ ግንባታን እና መሰረተ ልማት ማጋራትን ለማሳለጥ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር ይቀናጃል፤ እና

(መ) ገበያ መር አካሄድን በመከተል እና በማሻሻያው ጥቅማቸው ከሚጎዳ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር፤ ሊጋሩ የሚችሉትን የመሠረተልማቶችን ዝርዝር ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊወስን ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## አጠቃላይ መርሆዎች

### 6. አጠቃላይ የመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን መርሆዎች

ሁሉም የደራሽነት አገልግሎት ስምምነቶች ከሚከተሉት መርሆች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፡፡

1) ግልፅነት:

(ሀ) ከመሠረተልማት ማጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ውሳኔዎችን በሚመለከት ባለሥልጣኑ ውሳኔ ለመስጠት የሚከተላቸው ሂደቶች የሚታዩ እና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

(ለ) ሁሉም የደራሽነት አቅራቢ በባለሥልጣኑ የፀደቀውን የመሠረተ ልማት ማጋራት አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ እንዲታተም ማድረግ እና ለደራሽነት ፈላጊ ከክፍያ ነጻ በሆነ መንገድ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ የፀደቀውን የመሠረተ ልማት ማጋራት አቅርቦት ማጣቀሻ ሰነድ በድረ ገፁ ላይ ያወጣል፤

2) አድልዎ አለማድረግ;

አድልዎ ያለሚድረግ ሞሮህ የደራሽነት አገልግሎት አቅራቢ ለደራሽ ፈላጊ የሚያቀርበው የደራሽነት አገልግሎት አቅርቦት የወል ቃሎችና ሁኔታዎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ለራሱ ወይም በተመሳሳይ የንግድ ማሊያ ላይ ለሚገኝ ሌላ ኦፕሬተር ከሚያቀርብበት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡

3) ሕጋዊ ክፍያዎች

ለደራሽነት አገልግሎት የሚከፈሉ ክፍያዎች ትክክለኛ ፥ ምክንያታዊ እና ወጪ ማስረት ያደረገ መሆን አለባቸው።

## ክፍል አራት

## ኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት ማጋራት ሥርዐቶች

### 7. መብቶች እና ግዴታዎች

1) ሁሉም ደራሽነት ፈላጊዎች ከማንኛውም የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት አገልግሎት የማጠየቅ መብት አላቸው፤ እነዚህ አካላት በተጠቀሱት አገልግሎቶች የስምምነት የወል ቃሎች ላይ በቅን ልቦና መደራደር ይኖርባቸዋል፡፡

2) በባለሥልጣኑ የደራሽነት አገልግሎት ላይ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የተወሰነ የደራሽነት አቅራቢ፤ በደራሽነት ፈላጊ የኮሎኬሽን ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ መመለስ እስከተቻለ ድረስ መመለስ እና አገልግሎቱን በተመለከተ በቅን ልቦና እና ምክንያታዊ በሆኑ ደንብ እና ሁኔታዎች መደራደር አለበት።

3) የደራሽነት አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ኮሎኬሽንን ከተመለከተው ጥያቄ ወጪ ያሉ ሌሎች ጥያቄዎችን የሚከተሉትን ምክንያቶች ማስረት በሚድረግ ወድቅ ሊያደርጋቸው ይችላል፦

(ሀ) በቂ የሆነ አቅም ወይም ቦታ አለመኖርን፤

(ለ) ሕገወጥነትን፤

(ሐ) ደህንነትን፥ አስተማማኝነትን እና የመገልገያ ማሳሪያ አለመጣጣምን ወይም

(መ) ከኢኮኖሚ ወይም ከቴክኒክ አንጻር ተግባራዊ ሆነ አለመቻልን።

### 8. በቅን ልቦና የሚደረግ ድርድር

1) የደራሽነት አገልግሎቶች ስምምነት ላይ በሚስተፉ ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ድርድር በቅን ልቦና መካሄድ አለበት፡፡ ከደራሽነት ጋር የተያያዙ አለመግባባቶች የተከሰቱ እንደሆነ አለመግባባቶችን በሙሉ ለመፍታት ተገቢውን ጥረት ሚድረግ አለባቸው፡

2) በቅን ልቦና በሚደረጉ ድርድሮች ላይ እያንዳንዱ ተደራዳሪ ፤-

(ሀ) ሌላኛውን ወገን ሆን ብሎ ማሳሳት፤

(ለ) ለስምምነቱ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ጨምሮ ወጪን ለማስላት እና የሚፈለጉ መግለጫዎችን ለማየት የሚረዱ መረጃዎችን ለማስጠት አለመፈለግ።

(ሐ) ሌላኛውን ወገን በኃይል ወይም በመጫን ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማስገደድ፤ ወይም

(መ) ሆን ብሎ ድርድርን መደናቀፍ ወይም ማዘግየት፤

የለበትም።

3) የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም በቅን ልቦና የመደራደር መርሆዎችን እንደመጣስ ያስቆጥራል፤

(ሀ) ለሌላው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ተገቢነት ያላቸውን እና ለሚፈለገው አገልግሎት የሚውሉ ሁሉንም መረጃዎችን አለማስጠት፤

(ለ) ወጪን መሰረት ያላደረገ ክፍያን መጠየቅ፤

(ሐ) ምክንያታዊ ያልሆኑ ደንቦች እና ሁኔታዎችን ማቅረብ፤

መ) ጫና የሚያሳድሩ ወይም ያለአግባብ የተለጠጡ ወይም ገደብ የሚጥሉ ሚስጥርን ያለመግለጽ ስምምነቶችን እንዲፈረም መጠየቅ፤

(ሠ) ለወደፊት ማሻሻያዎችን ለማድረግ የሚፈቅድ ድንጋጌ በስምምነት ወስጥ እንዲካተት አለመፍቀድ፤

(ረ) በስምምነቱ ወስጥ የተካተቱትን የወል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ከጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ ጉዳዮችን እልባት ከማስጠት ጋር ለማያያዝ መጣር፤

(ሰ) ገዥ ወሳኔዎችን ለመፈጸም ሥልጣን ያለውን ሰው ለማስየም በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አለመሆንን ጨምሮ እና በዚህም ሳይወሰን ድርድርን የማዘግየት ድርጊቶችን መፈጸም፤ እና

(ሸ) በባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው መሠረት በቅን ልቦና የመደራደርን መርህ ይጥሳሉ ብሎ ሊቆጥራቸው የሚችላቸውን ሌሎች ድርጊቶች መፈጸም፡፡

## 9. የመሠረተልማት መጋራት እና/ወይም ኮሎኬሽን አገልግሎቶችን መጠየቅ

1) አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የደራሽነት አገልግሎት ጥያቄን ለሌላ ኦፕሬተር ሲያቀርብ ጥያቄውን በሚከተለው መልክ ያቀርባል፤

(ሀ) በጽሑፍ ለተጠየቀው ኦፕሬተር ማቅረብ፣

(ለ) ድርድሩን ለመጀመር የታሰበበትን ቀን፣ የደራሽነት አገልግሎት የሚፈለግበትን ቀን እና የቴክኒክ ማስፈርቶችን ጨምሮ እና በእነዚህም ሳይወሰን ከተጠየቀው የደራሽነት አገልግሎት ዓይነት ጋር የተያያዙ የተሟሉ መረጃዎችን ማካተተ፤ እና

(ሐ) ስለአቀረበው ጥያቄ በአምስት (5) የሥራቀናት ወስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ፡፡

2) የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ፈላጊ ጥያቄ በደረሰው በ10 የስራ ቀናት ወስጥ፦

(ሀ) ከደራሽነት አገልግሎት ጋር የተያያዙ ደርድሮችን በታቀደው ቀን መጀመር፤

(ለ) የተጠየቀወን የደራሽነት አገልግሎት ዓይነት ማቅረብ፤ እና

(ሐ) በደራሽነት ጠየቂ የግዜ ሰሌዳ ወስጥ የደራሽነት አገልግሎት ማስጠት ፤

መቻል ወይም አለመቻሉን ለጠየቂው ኦፐሬተር በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

3) የደራሽነት አቅራቢ የተጠየቀወን የደራሽነት አገልግሎት ማስጠት የሚችል መሆኑን ለደራሽነት ጠየቂው ከገለጸ፦

ሀ) የጸደቀወን የደራሽነት አቅርቦት ማጣቫ ሰነድ ቅጂን ማስጠት፤

ለ) የደራሽነት ጠየቂወን የቦታ ምልከታ እንዲያደርግ መፍቀድ እና

ሐ) የደራሽነት ጥያቄ በቀረበ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ድርድሩን መጀመር፤ ይኖርበታል፡፡

4) የደራሽነት አቅራቢ እና የደራሽነት ፈላጊ ኦፕሬተር በቅን ልቦና መደራደርና ድርድሩን ለማጠናቀቅ የሚቻላቸወን ሁሉ ጥረት በማድረግ ድርድሩ በተጀመረ ከአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ወስጥ መፈራረም ይኖርባቸዋል፡፡

5) የደራሽነት አቅራቢ እና የደራሽነት ፈላጊ የደራሽነት ስምምነት ለመተግበር የሚያስችሉ ማልገያ ማሪያዎች እና የቅጥር ግቢ ሁኔታዎች የደራሽነት ስምምነት በተፈረመ ከሠላሳ (30) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ወይም ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙበት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ወስጥ ማጠናቀቃቸወን ሚረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

6) የደራሽነት ጥያቄ ወድቅ የሚሆነው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 7 (3) በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ሲሆን የደራሽነት አቅራቢ ጥያቄወን ወድቅ ያደረገበት አሳማኝ ምክንያትን የደራሽነት አገልግሎት ጥያቄን በተቀበለ ከአስር (10) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

7) የደራሽነት አቅራቢው የደራሽነት አገልግሎት ጥያቄ ወደቅ የተደረገበትን ቅጂ ለደራሽነት ፈላጊው በደረሰው ከአምስት (5) የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል ወስጥ እንዲያያዝ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

8) በአዋጁ አንቀጽ 44 (4) እና 44(9) መሠረት ባለሥልጣኑ የደራሽነት አቅራቢው ለተጠየቀው የደራሽነት አገልግሎት አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ እንደሆነ እና ተዋዋይ ወገኖቹ ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ወስጥ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ከተዋዋዮቹ አንዱ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ በመግባት በአዋጁ ከአንቀጽ 35 እስከ አንቀጽ 38 ወይም መጣትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት አስገዳጅ ወሳኔ ማስጠት ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የደራሽነት ስምምነቶች

### 10. የደራሽነት ስምምነቶች

1) ሁሉም የመድረስ ስምምነቶች በጽሑፍ ሆነው፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገገወን መርሆዎች የተከተሉ፣

(ለ) በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ፈቃዶች የተመለከቱትን የወል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን የሚያከብሩ፣

(ሐ) በኢንዱስትሪው በስፋት ተቀባይነት ያገኙ ወይም በባለሥልጣኑ የፀደቁ ደረጃዎችን የሚያሟሉ፤ እና

(መ) ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ እና በባለሥልጣኑ ከወጣ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ጋር የተጣጣሙ፤

መሆን ይኖርበታል፡፡

2) የደራሽነት ስምምነት የደራሽነት ፈላጊ እና የደራሽነት አቅራቢ ህጋዊ በሆነ መንገድ ማስጠት የሚችሉትን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገድብ ወይም እንዳይፈጸም የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

### 11. የደራሽነት ስምምነቶችን ፋይል ስለማድረግ

1) የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ስምምነት የኤሌክትሮኒክ ቅጂን ስምምነቱ በተፈረመ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ በባለሥልጣኑ ፋይል እንዲያያዝ ማድረግ አለበት፡፡

2) ባለሥልጣኑ ፋይል በተደረገው የደራሽነት ስምምነት ወስጥ የተካተቱትን የወል ቃሎች እና ሁኔታዎችን ማገምገም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በራሱ ሥልጣን ከተዋዋይ ወገኖቹ ከአንዱ ተጨማሪ ሚጃዎች ማጠየቅ ይችላል፡፡

### 12. የደራሽነት ስምምነቶች ማሻሻያ

1) ፋይል የተደረገወን የደራሽነት ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች በጋራ ስምምነቱን ማሻሻል ወይም ማስተካከል ይችላሉ፡፡ የተሻሻለው ወይም የተስተካከለው ስምምነት በተፈረመ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ከባለሥልጣኑ ፋይል ጋር መያያዝ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ፋይል የተደረገው የደራሽነት ስምምነት ተዋዋይ የሆኑ ወገኖች ስምምነቱን በሚያሻሽሉት ወቅት የወል ቃሎች እና ሁኔታዎች ላይ ማስማማት ያልቻሉ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ከተዋዋይ ወገኖቹ በአንዱ ጥያቄ ወይም በራሱ ሥልጣን ጣልቃ በመግባት አለመግባባትን ለመፍታት በወጣው መመሪያ መሠረት የወል ቃሎችን ወይም ሁኔታዎችን መወሰን ይችላል።

## 13. <u>የደራሽነት ስምምነትን ማቋረጥ</u>

1) የደራሽነት ስምምነት የሚቋረጠው በስምምነቱ የተመለከቱትን የወል ቃሎች በጥብቅ በመከተል ነው፡፡

2) በባለስልጣኑ ዘንድ የተያያዘን የደራሽነት ስምምነትን ማቋረጥ የፈለገ ተዋዋይ ወገን የወሉን ማቋረጫ ምክንያቶች በመጥቀስ ለሌላው ወገን ከስልሣ (60) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ ማሣወቅ እና በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

3) የተፈጸመ ጥሰት በሚኖርበት ወቅት ማስጠንቀቂያ ሰጪው ኦፕሬተር ለሌላው ተዋዋይ ወገን ጥሰቱን እንዲያስተካክል ከሠላሣ (30) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዚህ ጊዜ ወስጥ ማስጠንቀቂያ የደረሰው ወገን ጥሰቱን ካላስተካከለ ማስታወቂያ የሰጠው ወገን ተጨማሪ ሰላሳ (30) የስራ ቀናት የወል ማቋረጫ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስምምነቱን ያቋርጣል ወይም በባለሥልጣኑ ሙት መፍቻ መመሪያ መሠረት ጣልቃ እንዲገባ ማጠየቅ ይችላል፡፡

4) የደራሽነተ ስምምነት ለቋረጥበት እንደሆነ ማስጠንቀቂያ የተላከለት ደራሽነት ፈላጊ ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ ሊጠይቅ ይችላል። በዚህ ግዜ ባለስልጣኑ የሙት መፍቻ መመሪያን መሠረት በማድረግ ጣልቃ ይገባል፡፡

5) የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ስምምነትን ያቋረጠ ከሆነ ፤ ስምምነቱ በተቋረጠ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ እና የስምምነት ማቋራጫ ማስታወቂያ ቅጂ ለባልሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

## 14. <u>የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ</u>

1) የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተደነገጉትን የደራሽነት ስምነቶችን አጠቃላይ መርሆዎች እና የዚህን መመሪያዎች ድንጋጌዎችን መከተል እና የሰነዱ አካል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2) ለደራሽነት አገልግሎቶች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳላቸው በባለሥልጣኑ የተወሰነላቸው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች በሙሉ የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ እንዲያደቅላቸው በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለባቸው፡፡ የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡ መመሪያ ከሰጠበት ከሰላሳ (30) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ፋይል መደረግ አለበት፡፡

3) ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድን ለማግማም እና ለህትመት ብቁ መሆኑ አለመሆኑን ለመወሰን ወይም በቀረበው ሰነድ የተካተቱትን የወል ቃሎች ወይም ሁኔታዎች ጣልቃ በማባባት ለማሻሻል ከሃያ (20) ቀናት የበለጠ ጊዜ መውሰድ የለበትም፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ በሃያ (20) ቀናት ወስጥ ወደቅ ካላደረገው ወይም ጣልቃ በማባባት ካልቀየረው የቀረበው ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

4) በባለሥልጣኑ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር፣ የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ የተሻሻለ ሰነድ እስከሚፀድቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡ የፀደቀ የደራሽነት ሰነድ በባለሥልጣኑ ድረ ገጽ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

5) የፀደቀ የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ የያዘ የደራሽነት አቅራቢ የተሻሻለውን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነዱ እንዲፀድቅ በባለሥልጣኑ ዘንድ ፋይል ማድረግ አለበት፡፡

6) ባለሥልጣኑ የተሻሻለውን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ በማግምም ለጸድቅ እና ለህትመት ብቁ መሆን አለመሆኑን በአስር (10) የስራ ቀናት ወስጥ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲጸድቅ የቀረበውን ጥያቄ ወደቅ ካላደረገው ወይም ሰነዱን በአስር (10) የስራ ቀናት ወስጥ ጣልቃ ገብቶ ካላሻሻለው የተሻሻለው የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ እንደፀደቀ ይቆጠራል፡፡

7) ባለሥልጣኑ እርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ፤ የወል ቃሎች እና ሁኔታዎች የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ፡-

   (ሀ) የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ ወይም የሰነዱ ማሻቸውም ድንጋጌ ከአዋጁ፣ ከዚህ መመሪያ ወይም በባለሥልጣኑ ከፀደቀ ተፈጻሚነት ካለው ማናቸውም መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ወይም

   (ለ) ባለሥልጣኑ ጣልቃ መግባቱ ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፡፡

በራሱ ሥልጣን ወይም ከቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጣልቃ በማባባት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

8) ባለሥልጣኑ በእርሱ ዘንድ ፋይል የተደረገውን ወይም የፀደቀውን የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድ ለማሻሻል ጣልቃ ለማባባት ከወሰነ በአዋጁ አንቀጽ 36 እና አንቀጽ 37 መሠረት እና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሥነስራዓቶችን በመከተል ተገቢ የሆኑትን ማሻሻያዎች ግልጽ በሆነ መንገድ መወሰን ይኖርበታል፤

   (ሀ) መደበኛ የአሠራር ሂደትን በመከተል የደራሽነት ማጣቀሻ ሰነድን ለማሻሻል ማዘጋጀቱን ለሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት በጉዳዩ ያገባኛል ለሚሉ ወገኖች ያሳውቃል፡፡ ማስታወቂያውም የትኛው ድንጋጌ እንደሚሻሻልና ለምን እንደሚሻሻል የሚያሳይ ግልጽ የሆነ ማብራሪያ የያዘ ሆኖ ሰነዱ፤

      (1) በአዋጁ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤

      (2) ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም

      (3) በባለሥልጣኑ በፀደቀ ተፈጻሚነት ባለው መመሪያ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን መሆኑን፤ ወይም

(4) የሕዝብን ጥቅም የሚያስጠበቅ መሆኑን፤

ማሳየት ይኖርበታል፡፡

(ለ) የሕዝብ ማስታወቂያው በማሻሻያነት የቀረበውን ሃሣብ እና የማሻሻያውን አሳማኝ ምክንያቶች ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ሐ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በማሻሻያ ሃሣቡ ላይ ምላሽ እና አስተያየት እንዲሰጡ ከአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ያላነሰ ጊዜ ማስጠት ይኖርበታል፡፡

(መ) ባለሥልጣኑ በጉዳዩ ያገባኛል ከሚሉ ወገኖች አስተያየት ከተቀበለ በኋላ በተቀበለው አስተያየት ላይ ምላሹን ከአስራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ማስጠት ይኖርበታል፡፡ በምላሹም፤

(1) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በማስጠት የሚጨረሻ ውሳኔውን ያሰፍራል፤ ወይም

(2) ለእያንዳንዱ አስተያየት ምላሽ በማስጠት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው ሃሣብ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የሚጨረሻ ውሳኔ ከማስጠቱ በፊት በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች በመጀመሪያው ዙር በተቀመጠው ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንደገና አስተያየት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

(ሠ) ባለሥልጣኑ የሚጨረሻ ውሳኔውን ከማስጠቱ በፊት በራሱ ሥልጣን ከሁለት ለበለጡ ዙሮች በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ማሻሻያዎች ወይም አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

(ረ) በቀጥጥሩ ሂደት ባለሥልጣኑ በተቀበለው አስተያየት ላይ የሰጠውን ምላሽ እና የሚጨረሻውን ውሳኔ በድኅረ ገጹ ማውጣት ይኖርበታል፡፡

(ሰ) በቁጥጥሩ ሂደት በጉዳዩ ያገባኛል በሚሉ ወገኖች ለባለሥልጣኑ የተሰጡ መረጃዎች ሚስጥራዊነትን በተመለከተ ባለሥልጣኑ የመረጃዎቹን ሚስጥራዊነት ለማጠበቅ ተገቢውን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

9) የደራሽነት ማጥቀሻ ሰነድ የቀረቡ የደራሽነት አገልግሎቶች፣ የቴክኒክ ደረጃዎች እንዲሁም በደራሽነት አገልግሎት አቅራቢ የሚተገበሩ የደህንነት ደረጃዎች ዝርዝር የውል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

10) የደራሽነት ማጥቀሻ ሰነድ የአገልግሎቱ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሻሻሉ የሚገልጽ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት፡፡

11) የደራሽነት ማጥቀሻ ሰነድ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

(ሀ) የስምምነት ሚቀፍ፤

(ለ) የሚቀርቡ የደራሽነት አገልግሎቶች መግለጫ እና ተያያዥ የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

(ሐ) በደራሽነት አቅራቢ የሚዟገበሩ የደህንነት ደረጃዎችን ጨምሮ በደራሽነት አቅራቢ በባለቤትነት ወደ ተያዙ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ወደ አሉ ዝግጅቶች ወይም ቁሳዊ መሠረተ ልማት ለመግባት የሚያስችሉ ዝርዝር የወል ቃሎች እና ሁኔታዎች፤

(መ) የአገልግሎት አሰጣጥን፣ዕቅድን እና ጥገናን ጨምሮ የአሠራር ሥርዐቶች፤

(ሠ) ክፍያዎች፣ የክፍያ ማጠየቂያ ሥርዐቶች እና የወል ቃሎችና ሁኔታዎች ጨምሮ ንግድ ነክ ጉዳዮች እንዲሁም የሜት ኪራይ ወጪዎች፥ የማጠናከሪያ ስራዎች እና ሌሎችም፤

(ረ) የአገልግሎት አሰጣጥ ስምምነት፤

(ሰ) ለኮሎኬሽን ወይም ለመሠረተ ልማት መጋራት ያለውን ቦታ ስፋትን ጨምሮ የአገልግሎቶች ማጠንና አቅም ሚዟጃዎች እንዲሁም ለተቀጥላ አገልግሎቶች ወይም ዝግጅቶች የቴክኒክ ማስፈርቶች ልወውጥን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፤ እና

(ሸ) የደራሽነት ፈላጊዎች የወል ቃሎችን እና ሁኔታዎችን ለማሻሻል የቀረቡ ሃሣቦችን እና ማሻሻያዎቹ የሚከናወንበትን የጊዜ ገደብ የሚያወቁበትን መንገድ ጨምሮ የማሻሻያ ሥርዐቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች፡፡

## ክፍል ስድስት

## ኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት መጋራት ክፍያዎች እና ወጪዎች

### 15.የመሠረተ ልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን አገልግሎቶች ክፍያዎች

1) የደራሽነት አቅራቢ ከደራሽነት ጠያቂ ይልቅ ከእርሱ ጋር የቅርብ ትስስር ላለው ደርጅት የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ዋጋ ወይም ሁኔታዎች ማስጠት አይችልም።

2) የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት አገልግሎትን ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ ማቅረብ ያለበት ሲሆን በሌላ የደራሽነት አቅራቢ ለእሱ ከሚሰጠው የደራሽነት አገልግሎት ዋጋ ያነሰ ጥቅም የሚሰጥ መሆን የለበትም።

3) ለደራሽነት አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎች፤

(ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተደነገገው መርሆዎች መሠረት የሚሟሉ፤

(ለ) ለተጠየቀው አገልግሎት የግድ አስፈላጊ ላልሆኑ የደራሽነት አገልግሎቶች ደራሽነት ፈላጊው ክፍያ እንዳይፈጽም እያንዳንዱን አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ተነጣጥለው የተደራጁ እና

(ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 44(3) እና 44 (8) ማሰረት ድርድር እና ስምምነት የተደረገባቸው

መሆን አለባቸው፡፡

4) የደራሽነት አገልግሎት ክፍያዎች ተለይተው፤

(ሀ) የደራሽነት አገልግሎቶች ለመጀመር እና ተግባራዊ ለማድረግ ቋሚ የአንድ ጊዜ ክፍያዎች፤

(ለ) ጥቅም ላይ እየዋለ ላለ የኔትወርክ መሠረተልማት ወይም መገልገያዎች በየጊዜው የሚከፈሉ ክፍያዎች እና

(ሐ) ለተጨማሪ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ተለዋዋጭ ክፍያዎች፤

ራሳቸውን ችለው መቅረብ ይኖርባዋል፡፡

5) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3(ሐ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 44 መሰረት ለደራሽነት አገልግሎት ክፍያን ሊወስን ይችላል።

## 16. የሂሳብ ደብተር ማስያየት

1) ባለሥልጣኑ የደራሽነት አቅራቢው ለደራሽነት አገልግሎት አግባብነት ባለው ገበያ ወስጥ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ እንደሆነ እና የደራሽነት አቅራቢው በተጨማሪ የችርቻሮ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶችን በችርቻሮ የሚሸጥ ከሆነ፣ ከዚህ አገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ወጪዎችና ገቢዎች ለማየት ለሚጠቀሙ የደራሽነት አገልግሎቶች በሕግ መሠረት ራሱን ችሎ እንደሚሰራ ከባንያ የተለዩ የሂሣብ መዝገቦችን መያዝ ይኖርበታል፡፡

2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የሂሳብ አያያዝ እንዴት ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት የሚያሳይ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለምደባ፣ አቅም ይዞ ስለማቆየት እና ደራሽነት ማግኘት

## 17.አቅምን ስለመመደብ እና ይዞ ስለማቆየት

1) የደራሽነት አገልግሎትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በደራሽነት አቅራቢ የሚስተናገዱትና አገልግሎቱም የሚሰጠው ቀደሞ የመጣ በቅድሚያ ያገኛል የሚለውን መርህ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ቀደሞ የመጣ ቅድሚያ ያገኛል የሚለው መርህ በአንድ ግዜ የሚመጡ ጥያቄዎችን በእኩልነት ፣ አድሎ በሌለበት ሁኔታ እና ወጥነት ባለው ሚዛን ከማየት መከልከል የለበትም።

3) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የቴሌኮሚኒኬሽን መገልገያን ሲያስፋፋ እንዲሁም ለመሰረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን የሚሆኑ መሰረተ ልማቶችን ሲተከል ያለውን የመሰረተልማት መጋራት እና የኮሎኬሽን ፍላጎት ግንዛቤ ወስጥ መክተት አለበት።

4) ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን መገልገያ ተጨማሪ የመሰረተልማት መጋራት እና ኮሎኬሽን ጥያቄዎችን ማስተናገድ የሚያስችል ካልሆነ ቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩ ያለውን የመገልገያ አቅም ለማጨመር ሚሉሶ ሚልማትን ግንዛቤ ወስጥ ሊከት ይገባል።

5) ለመጋራት የሚውሉ መሰረተልማቶችን የሚዘረጋ ወይም ለማዘርጋት እቅድ ያለው የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ደራሽነት ፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ አካላትን መስፈርቶቻቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ ሊጠይቃቸው ይችላል። በሁለቱ መካከል እንደሚስማሩው ስምምነት ለመጋራት የሚሆነውን መሰረተልማት ማስፋፊያ ወጪ ሊካፈሉ ይችላሉ።

6) ቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር የረጅም ግዜ ኢንቨስትመንትን ማስረት በሚድረግ አቅምን ይዞ የማቆየት መብት ሁልግዜ ቢኖረወም፤ ይህ ሁኔታ አዲስ ወደ ገበያ የሚቀላቀሉ አገልግሎት ሰጪዎች የኔትዎርክ የማስፋፊያ አቅድን እንዳያደናቅፍ ሚዛኑን ማጠበቅ አለበት።

7) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወሰን አቅም ኖሮት የደራሽነት አገልግሎት አቅምን ይዞ የመቆየት አሚራጭን ተግባራዊ ሲያደርግ፤

ሀ) አቅሙን ይዞ ሟቆየት የሚቻለው ከ ሁለት (2) ዓመት ላልበለጠ ግዜ ነው። ከዛ በሆላ አቅሙን ይዞ የመቆየት መብቱ ያበቃ እና ለደራሽነት ፈላጊዎች ክፍት ይሆናል፤

ለ) ይዞ መቆየት የሚቻለው አቅም ካሉት እያንዳንዱ ማስረተ ልማት ወስጥ ከ25% ያልበለጠውን ነው።

8) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሩ አቅምን ይዞ መቆየትን የተማለከተ ኢንፎርሜሽን እና የሰነድ ማስረጃዎች ሚደራጀት እና አስፈላጊ በሆነበት ግዜ ሁሉ ለሌሎች ኦፕሬተሮች ተደራሽ መሆን አለበት።

## 18.ለአዲስ መሠረተልማት ተደራሽነትን የሚረጋገጥ ግዴታ

1) አዲስ የኔትወርክ ማስረተልማት ወይም ማልገያዎችን ለማንባት ሲታቀድ እና ሲገነባ፣ ሁሉም የደራሽነት አቅራቢዎች ወቅታዊ የኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት መጋራት ፍላጎት ወይም አዲሱን የኔትወርክ ማስረተልማት ወይም ማልገያዎች ማስፋፊያን ወይም ግንባታን ተከትሎ ወደፊት የሚኖረውን የኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት ሞጋሪያ ፍላጎትን በተገቢው ማጠን ከግምት ወስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ አዲሱ መሠረተ ልማት የሚዘቀደው እና የሚነባው ከደራሽነት ፈላጊዎች ጋር የሚደረገውን የኮሎኬሽን እና የመሠረተልማት መጋራትን በዚህ መሜያ ማስረት ለማስለጥ መሆን አለበት፡፡

2) አዲስ ቋሚ ማስረተልማት እና ማልገያዎችን ለማዘርጋት ወይም ለማንባት የሚቅድ የደራሽነት አቅራቢ ለወደፊቱ እነዚህን ቋሚ ማስረተልማት እና ማልገያዎችን ማጠቀም/መድረስ ይፈልጋሉ ተብለው ምክንያታዊ በሆነ ማንገድ ለሚገሰቡ ቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የልማት ዕቅዱን ማጋራት አለበት፡፡

3) የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወቅታዊ ወይም ወደፊት ይኖራሉ ተብሎ የሚገሰቡ የደንበኞች ፍላጎትን ለማሟላት የሚጠቅሙ ገመዶችን፣ ማሪያዎችን ወይም ሌሎች ማልገያዎችን ማዘርጋት የለበትም እንዲሁም ተገቢ ባልሆነ ቦታ አጠቃቀም ምክንያት ካሉትም ሆኑ እና ወደ ፊት ሊማጡ ከሚችሉ የደራሽነት ፈላጊዎች ጋር የሚደረግ የኮሎኬሽን እና መሠረተልማት መጋራትን ማከልከል ወይም ማደብ የለበትም።

4) የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ስምምነትን የሚማለከቱ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ክፍሎችን ወይም ማልገያዎችን ለማሻሻል፣ ለማስፋፋት ወይም ቦታ ለመቀየር ያቀደ እንደሆነ የታሰበውን ለውጥ በማለጽ ለወጡ ደራሽነት ፈላጊ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን የደራሽነት አገልግሎት ማስተጓጎልን ለመቀነስ ከታቀደ ዕቅድ ጋር ከዘጠና (90) የሥራ ቀናት ያላነሰ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖች ማስጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ግዴታን ስለማሟላት

## 19.ግዴታ እንዲሟላ ስለማጠየቅ

1) በዚህ መመሪያ የተገለጸ ማቸወም ድንጋጌ ቢኖርም፣ የደራሽነት አቅራቢ በዚህ መመሪያ የተጣለበትን የተወሰነ ግዴታ እንዳላላለት ባለሥልጣኑን ማጠየቅ የሚችለው፤

(ሀ) ባለሥልጣኑ የደራሽነት አቅራቢን በደራሽነት አገልግሎቶች አግባብ ባለው ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ያልወሰነ እንደሆነ፤

(ለ) ምንም እንኳን ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው የደራሽነት አገልግሎቶች ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ ቢሆንም የነበረው ወድድር በማወጡ የደራሽነት አቅራቢው ቀደም ሲል የነበረውን የገበያ ድርሻ ያጣ እንደሆነ፤

(ሐ) ምንም እንኳን ባለሥልጣኑ አግባብ ባለው የደራሽነት አገልግሎቶች ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የወሰነ ቢሆንም በተወሰነ ሜልከዓ ምድር አካባቢ በተወሰኑ ሁኔታዎች የሚፈረገው ወድድር በሜልከዓ ምድሩ አካባቢ የግዴታዎች ማላላትን የሚጠይቅ የሆነ እንደሆነ፤ ወይም

(መ) በአንድ የተወሰነ የኔትወርክ ማስረተልማት ክፍል ወይም አገልግሎት ወስጥ ያሉ ሁኔታዎች በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ግዴታዎችን አሟልተው ወደ ተግባር ለማወጥ ወይም አዋጪ ለማድረግ ያላስቻለ እንደሆነ ነው፡፡

2) ግዴታዎች እንዲላሉለት ለባለሥልጣኑ ጥያቄ ያቀረበ የደራሽነት አቅራቢ የትኛው ግዴታ እና ከመመሪያው የትኛው አንቀጽ እንዲላላለት በመወሰን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርበታል፡፡

3) ባለሥልጣኑ ግዴታዎች እንዲላሉ በጽሐፍ ለቀረበው ጥያቄ ከሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ወስጥ፤

((ሀ) ከተገቢው ማበራሪያ ጋር ጥያቄው ወድቅ መሆኑን፤

(ለ) ጥያቄውን ለማምገም ተጨማሪ ሚጃ የሚፈልግ መሆኑን፤ ወይም

(ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 34 እና 36 እስከ አንቀጽ 38 በተደነገጉት ሥነ ሥርዐቶች መሠረት ጉልቃ በመግባት አስገዳጅ ወሳኔ ለማጠት የወሰነ መሆኑን፤

በመግለጽ ምላሽ ማስጠት ይኖርበታል፡፡

4) የዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ባለሰልጣኑ ግዴታ ይላላልኝ የሚል ማመልከቻን ማቅረብ የሚቅደው ለአዲስ የቴሌኮሚኬሽን ኦፐሬተር ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከአምስት (5) ዓመት በኋላ ነው።

5) ባለሥልጣኑ ለአንድ የደራሽነት አቅራቢ በዚህ መመሪያ የተመለከተው የተወሰነ ግዴታ እንዲላላለት ሲወስን ይህ የግዴታ ማላላት የሚቆየው ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለኮሎኬሽን

## 20. ኮሎኬሽን የኢንተርኮኔክሽን አካል ስለመሆኑ

1) የኮሎኬሽን አገልግሎት ለኢንተርኮኔክሽን አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ የኮሎኬሽን የወል ቃል እና ሁኔታዎች በኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ወስጥ መካተት አለባቸው። እነዚህ የወል ቃሎች እና ሁኔታዎች በዚህ መመሪያ መሰረት ማዘጋጀት አለባቸው።

2) ባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የኮሎኬሽን አገልግሎቶች ላይ አለው ብሎ የወሰነው የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተር በማስረተልማት መጋራት ማጣቀሻ ሰነድ ላይ ያሉትን ለኮሎኬሽን የሚሆኑ መልገያዎችን እና የኮሎኬሽን ክፍሎች ዋጋ ዝርዝሮችን አካቶ ማቅረብ አለበት፡፡

3) ከሌላ ኦፕሬተር ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚፈልግ ኦፕሬተር ለሥራው ተስማሚ የሆነውን የኮሎኬሽን ዓይነት የመምረጥ ነፃነት አለው፡፡ አባሪ "ሀ" የተለያዩ የኮሎኬሽን ዓይነቶችን ይገልጻል።

4) በግልጽ ተፈጻሚ እንዳይሆን ካልተደረገ በስተቀር፣ የኮሎኬሽን የወል ቃሎች እና ሁኔታዎች በአጠቃላይ በቅጽ "ለ" ላይ ለመሠረተ ልማት መጋራት በተመለከቱት ደንቦች ይገዛል፡፡

## ክፍል አሥር

## ስለሕትመት

## 21. በባለሥልጣኑ የሚታተም የመሠረተልማት መረጃ

1) ባለሥልጣኑ የደራሽነት አገልግሎት ላይ አግባብ ባላቸው ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ ባለው የደራሽነት አቅራቢ ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ሥር ያለ የኔትወርክ መሠረተ ልማት እና አገልግሎቶችን የሚመለከቱ የኔትወርክ መሠረተልማት እና መልገያዎች የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ በየጊዜው ያሳትማል ወይም መታተማቸውን ያረጋግጣል፡፡

2) ባለሥልጣኑ አንድን የደራሽነት አቅራቢን አግባብ ባላቸው ገበያዎች ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ከወሰነ የደራሽነት አቅራቢው፦

(ሀ) ከደራሽነት ጠያቂዎች እየተጋራ ያለውን፤ ወይም፣

(ለ) ለመጋራት ዝግጁ የሆኑትን፤

አገልግሎቶቹ እና መሠረተ ልማት በተመለከተ፤ ለባለሥልጣኑ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 2 የተካተቱት መረጃዎች ለደራሽነት ፈላጊዎች የተጋራ ቦታ ወይም አቅም፣ ለመጋራት ዝግጁ መሆን የሚችሉ ቦታዎች ወይም አቅሞች እና ሌሎችም አካቶ መያዝ አለበት።

4) ከባለሥልጣኑ የቀረበወን የጽሑፍ ጥያቄ ተከትሎ የደራሽነት አቅራቢ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን መረጃ ጥያቄው በቀረበ በሠላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5) ባለሥልጣኑ ለሌሎች የተጋሩ ወይም ለማራት ዝግጁ የሆኑ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን በተመለከተ ከደራሽነት አቅራቢ የተቀበለውን ሚጃ በራሱ ጊዜ በድኅረ ገጹ ሊያወጣው ይችላል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ከንዐስ አንቀጽ (1) እስከ (5)የተደነገጉት ቢኖሩም፣ ሁሉም የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሠረት በሰላሰ (30) የስራ ቀናት ወስጥ በባለቤትነት የያዙትን ወይም በቁጥጥራቸው ሥር ያሉትን የሁሉንም ማማዎች እና ምሶሶዎችን፥ የኮለኬሽን ቦታዎችን፥ መተላለፊያ ማስመሮችን፥ የጥቁር ፋይበር ማስመር፥ የኢንተርኮኔክሽን ቦታ ማልገያ ማሪያዎች፥ ቁፋሮ የተደረገባቸው ቦታዎች፥ ያሉ አቅሞች እና ቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች አካላዊ ትስስር የሚደርጉበት በኮለኬሽን ወስጥ የማገኝ ቦታ ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ዝርዝሩም ስለእያዳንዱ ረገኘም ቋሚ እና ማማ ቢያንስ የሚከተሉትን ሚጃዎች ማያዝ አለበት፤

(ሀ) የማማውን ቦታ ስለሚያመለክት የጂፒኤስ ማጠሚያዎች፣

(ለ) ማከላከያ አጥር ፣ብቸኛ ምክሰ(ሞኖፖል)፣ ጊድ ወዘተ ጨምሮ ስለማማው መዋቅር ዓይነት ኢንፎርሜሽን፤

(ሐ) ማማው ስለተሠራበት መሣሪያ፤

(መ) ከሜት በላይ ስላለው ከፍታ፤

(ሠ) ስለ ከፍተኛው የክብደት ማጠን፤

(ረ)የቦታውን ስፋት በካሬ ሜ  እና ሌሎች ባህርያትን ጨምሮ ስለሥራ ቦታው ዝርዝር/አቀማመጥ/፤

(ሰ) ከኃይል ማከፋፈያ፣ከጄነሬተሮች፣ወዘተ የተያያዘ ሚጃን ጨምሮ ስለኃይል ማገኛ፡፡

ሸ) የማማ የክብደት ማጠን፥ የአንቴና ቁጥር፥ በማልገያ ማሪያዎች የተያዙ ቦታዎች በካሬ ሜ  እና ወዘተ ወቅታዊ አጠቃቀም እና

ቀ) ትርፍ ወቅታዊ አቅም

7) አንድ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ማናኛውም አይነት አዲስ የማማ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ሊገነባ ከታሰበው ማማ ጋር በተያያዘ በዘህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (6) የተገለጹ ሚጃዎችን ስለትክክለኛነታቸው ሚጋገጫ በማስጠት በሣላሳ (30) የሥራ ቀናት ወስጥ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

8) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ (6) እና (7) መሠረት ከቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተሮች የተቀበለውን ሚጃ የሚይዝበት የሚጃ ቋት ያደራጃል ፣ያስተዳድራል፣ በጽሑፍ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊ ሚጃዎችን ለቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር በአሥራ አምስት (15) የሥራ ቀናት ወስጥ ማስጠት ይኖርበታል።

## ክፍል አሥራ አንድ

## አለማባባትን ስለመፍታት

## 22.የኮሎኬሽን እና የመሠረተ ልማት ማጋራት አለመግባባትን ስለመፍታት

1) በደራሽነት አቅራቢ እና ፈላጊ መካከል የደራሽነት አገልግሎት የተጠየቀበት አግባብነት ወይም ለደራሽነት አገልግሎት ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ማጠየቅን በተመለከተ አለመግባባት ከተፈጠረ ወይም ተዋዋይ አካለት ደራሽነትን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ተዋዋይ አከላት የገበቡትን ስምምነት ተግባራዊ ማድረግ ካልቻሉ፤ ከሁለቱ አካላት አንዱ ባለስልጣኑ አለመግባባቱ እንዲፈታ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል።

2) አለመገበባቱን እንዲፈታ ለባለስልጣኑ ጥያቄ ያቀረበው አካል፤ ጥያቄውን በጽሁፍ በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉበት ቀን ጀምሮ ከሠላሳ (30) የስራ ቀናት ባልበለጠ ግዚ ወስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል።

4) ባለሥልጣኑ ጣልቃ እንዲገባ የቀረበወን ጥያቄ ተከትሎ ጥየቄወን በተቀበለ ከአስር (10) የሥራ ቀናት ባላነሰ ጊዜ ወስጥ፤

(ሀ) ጣልቃ ለመግባት ወይም ላለመግባት ከመወሰኑ በፊት ከተዋዋይ ወገኖቹ ተጨማሪ ሚጃዎችን በማጠየቅ፤

(ለ) ጣልቃ ላለመግባት ከወሰነ ላለመግባት የወሰነበትን ከእነ አሳማኝ ምክንያቱ በጽሐፍ በማሳፈር፤ ወይም

(ሐ) በባለሥልጣኑ የመግት መፍቻ መመሪያ በተደነገጉት ሥነ-ሥርዓቶች መሠረት ጣልቃ ለመግባት መወሰኑን፤

ለጠየቂው ወገን ምላሽ ማጠት ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አሥራ ሁለት

## ሕግ ማስፈጸም እና ሕግ ማክበር

## 23. ሕግ ማክበር

ባለስልጣኑ ደራሽነት አቅራቢ እና ደራሽነት ፈላጊ የአዋጁ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን ማክበራቸውን ይቆጣጠራል።

## 24. ሕግ ማስፈጸም

1) ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ፥ አዋጁ እና ባለስልጣኑ ያጸደቃቸውን መመሪያዎችን ማስረት በማድረግ የደራሽነት አቅራቢ ወይም የደራሽነት ጠየቂ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ከወሰነ፤ በአዋጁ አንቀጽ 52 ማስረት እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርምጃው የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ ሊሆን ይችላል።
2) የዚህ አንቀጽ ንሁስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የሚያስቀምጣቸው መፍትሄዎች እና ቅጣቶች በአዋጁ አንቀጽ 52(6) መሠረት ፈቃድ ስለማስረዝ፣ እገዳ እና ሌሎች የአስተዳደር እርምጃዎች

እና ቅጣዮች እንዲሁም የቅጣት ማጠኖች ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል አስራ ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**23. ማሻሻያ**

ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አከላት ጋር በመማከር እና ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በማቸውም ጊዜ ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

**24.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ ___ ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______ ቀን ________________ 2013 ዓ.ም.

**ኢንጂነር ባልቻ ሪባ**

**የኢትዮጵያ ኮሚኒከሽን ባለሥልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## አባሪ ሀ

## የደራሽነት አገልግሎቶች መግለጫ

ባለስልጣኑ በሌላ ሚልኩ እስካልወሰን ድረስ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት የአገልግሎቶች ክፍሎች/ሚደቦች/ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የወል የደራሽነት አገልግሎት ዓይነቶችን የሚገልጹ ናቸው፡፡ የተወሰኑት አገልግሎቶች የደራሽነት አቅራቢ የመንገድ የማጠቀም መብት ማራትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡፡

1) **ኮሎኬሽን፡ –** የደራሽነት አቅራቢ በራሱ ኔትወርክ መሠረተ ልማት በቦታው፣ በአገልግሎቶቹ ወይም በቅጥር ግቢው ለደራሽነት ጠያቂ የሚያቀርበው አገልግሎት ነው፡፡ የደራሽነት ጠያቂ የራሱን የቴሌኮሚኒኬሽን ማስተላለፊያ መሣሪያዎችን ለመትከል ለማጠገን እና ለማካሄድ በሳምንት 24 ሰዓት ወይም 7 ቀናት ወደ ኮሎኬሽን ቦታ ወይም ክፍል መግባት ይችላል፡፡ የኮሎኬሽን አገልግሎት በተለያዩ ዘዴዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ሀ) **የተመደበ ኮሎኬሽን፡ –** የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ጠያቂ የቴሌኮሚኒኬሽን መሳሪያዎቹን እንዲዘረጋ ፍላጎቱን መሠረት አድርጎ የሚመድበው፣ ለይቶ የሚያዘጋጀው እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ነው፡፡

   ለ) **ተጎራባች ኮሎኬሽን፡ –**የደራሽነት አቅራቢ ካለው አገልግሎት ተጎራባች በሆነ ራሱን በቻለ ቦታ ሆኖ ተነጥሎ ባለ ተቋም ወስጥ ለደራሽነት ጠያቂ የሚያቀርበው ቦታ ነው፡፡

   ሐ) **ርቀት ያለው ኮሎኬሽን፡ –** የደራሽነት አቅራቢ ለመሠረተ ልማት ማራት እና ኮሎኬሽን ጠያቂ በታጠረ ወይም በተከለለ ሥፍራ ቦታ የሚያቀርብበት ሆኖ ቦታውም ካሉት የአገልግሎት መሣሪያዎች የራቀ አካባቢ ነው፡፡

   መ) **ማጣመር፡ –**የደራሽነት አቅራቢ ለደራሽነት ጠያቂ በወለል ላይ ባለ ቦታ ወይም ሚደርደሪያ መሣሪያውን ጎን ለጎን እንዲያስቀምጥ የሚያቀርበው ነው፡፡

   **ሠ) ቨርቹዋል ኮሎኬሽን፡ –**የደራሽነት አቅራቢ የደራሽነት ጠያቂ ከኮሎኬሽን ቦታ ጋር ቁሳዊ ተደራሽነት ሳይኖር ከደራሽነት አቅራቢ አገልግሎቶች ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር የሚያደርግበት ነው፡፡ የደራሽነት ጠያቂ የራሱን የማስተላለፊያ መሣሪያ ሊያቀርብ ወይም ከደራሽነት አቅራቢ ሊከራይ ይችላል፡፡ መሣሪያዎችን የሚዘረጋው፣ የሚያንቀሳቅሰው እና የሚጠግነው የደራሽነት አቅራቢ ነው፡፡ የደራሽነት ጠያቂ ለምናባዊ ኮሎኬሽን ቦታ ወይም መሣሪያ ተደራሽነት ወይም ግንኙነት አይኖረውም፡፡ ሆኖም በኤሌክትሮኒክ መንገድ የኮሚኒኬሽን መሣሪያውን ሊቆጣጠር ይችላል፡፡

## ቋሚ ማስረተልማት

2) **ቋሚ ማስረተልማት አገልግሎት፡** ገባሪ ላልሆነው የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትዎርክ ክፍል ተደራሽነትን የሚሰጡ የተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶችን የሚያካት ነው። የሚከተሉት ምሳሌዎች ለማሳያነት ቀርበዋል፡-

   **ሀ) ለማስተላፊያ ቱቦ የሚኖር ተደራሽነት፡ –** ሜሬት ለሜሬት የሚሄዱ ሽቦዎች ለተሸፈኑበት ወይም ለሚያልፉበት ኮንደዩቶች ወይም ቧንቧዎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው፡፡ የማስተላለፊያ ቱቦዎቹ ሽቦዎቹን

የሚከላከሉ እና ተጨማሪ ቁፋሮ ሳያስፈልግ ተጨማሪ ሽቦዎችን ለማስገባት ወይም ያለወን ለማውጣት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ለማስተላለፊያ ቱቦዎች የሚሆር ተደራሽነት የጥገና ማከናወኛ ትናንሽ ጉድጓዶችን/ማንሆሎች/ እና የእጅ ማስገቢያ ቱቦዎች/ ሃንድሆሎች/ ወይም ሕንፃዎች የመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎችን እንዲሁም ለኃይል እና ለአየር ማቀዝቀዣ አገልግሎቶች ተደራሽ የሚያደርጉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

**ለ) ለማማዎች እና ለረዣዥም ቋሚዎች የሚሆር ደራሽነት፡-** ጠየቂ የራሱን የማስተላለፊያ መሣሪያ እና ሽቦዎች ለማዘርጋት ዓላማ በደራሽነት አቅራቢ ባለባቤትነት እና ቁጥጥር ሥር ያለን ማማን እና ረዣዥም ቋሚን እንዲጠቀም የሚፈቅድበት አገልግሎት ነው፡፡ አገልግሎቱም ሕንፃዎችን፣ የሥራ ቦታዎችን፣ ኃይልን እና አየር ማቀዝቀዣን ለመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎች ተደራሽ የሚያደርጉትን ያካትታል፡፡

**ሐ) ጥቁር ፋይበር፡** –የደራሽነት አቅራቢ ለደራሽነት ጠየቂ የሚያከራየው ነጠላ ፋይበር ወይም የብዙ ፋይበሮች ስብስብ ነው፡፡ ሆኖም የደራሽነት አቅራቢ የማስተላለፊያ መሣሪያወን ከተከራየው ፋይበር ጋር ማያያዝ አይችልም፡፡ አገልግሎቱም የጥገና ማከናወኛ ትናንሽ ጉድጓዶችን እና የእጅ ማስገቢያ ቱቦዎችን፣ ሕንፃዎችን፣ የሥራ ቦታዎችን፣ ኃይልን ወይም የሥራ እና አየር ማቀዝቀዣን ለመሳሰሉ ተዛማጅ ግንባታዎች ተደራሽ የሚያደርጉትን ያካትታል፡፡

**መ) የኢንተርኮኔክሽን መዳረሻ ነጥቦች፡ –** እነዚህ ነጥቦች ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የቴሌኮሚኬሽን ኦፕሬተሮች ወደ ተገናኙበት አገልግሎቶች፣ የሥራ ቦታዎች ወይም ሕንፃዎች ተደራሽ የሚያደርግ ነው፡፡ አገልግሎቱ ማያያዣዎችን፣ ኃይልን እና የአየር ማቀዝቀዣን ሊያካትት ይችላል፡፡

## <u>ገባሪ መሰረተልማት</u>

3) **ገባሪ መሰረተ ልማት፡** ገባሪ ለሆነው የቴሌኮሚኬሽን ኔትዎርክ አካል ወይም ክፍል ተደራሽነትን የሚሰጡ የተለያዩ ዓይነት አገልግሎቶችን የሚያካት ነው። የሚከተሉት ምሳሌዎች ለማሳየት ቀርበዋል፡-

ሀ) **የጅምላ የአቅም ኪራይ አገልግሎት፡** አስቀድሞ በተመሰረተ አቅም እና በአግባቡ በሚሠራ የኔትዎርክ ማስተላላፍ አገልግሎት አማካኝነት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚፈረግ የማስተላለፍ አገልግሎት ነው።ይህ አገልግሎት የረጅም ርቀት ማስተላለፊያ ኪራይን እንዲሁም የኢንተርኔት የማስተላለፍ አገልግሎትን ሊጨምር ይችላል።

ለ) **የሬዲዮ መዳረሻ ኔትዎርክ መጋራት፡-** የኔትዎርክ ግንኙነቱ የተለያየ ቅርፅ ሊኖረው ይችላል ለምሳሌ አንድ የሬዲዮ መዳረሻ ኔትዎርክ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ዋና የኔትዎርክ ባለቤቶችን ያስተናግዳል።ሌላው መንገድ ደግሞ የሬዲዮ መዳረሻ ኔትዎርክ አካልን ሊያካት ይችላል።

ሐ) **ብሔራዊ የሮሚንግ የጅምላ አገልግሎት፡** የደራሽነት ጠያቂ ሞባይል ኦፕሬተር ደንበኛ በተጠየቂ የሞባይል ኦፕሬተር ኔትዎርክ ላይ እንዲስተናገድ ሜድረግ ሲሆን በዚህም ደንበኛው የራሱ ኦፕሬተር የኔትዎርክ ተደራሽነት በሌለው አከባቢ ላይ አገልግሎት እንዲያገኝ ያስችለዋል።

መ) **ከፍተኛ የሚከተላለፍ አቅም ያላቸው ማስመሮችን ማራት፡** የአገልግሎት ዓይነት ሲሆን ማስረተልማት ማሪያ አቅራቢ እና የማስረተልማት ማሪያ ፋላጊ ከሬዲዮኖቻቸው እና ከዋና ኔትዎርክ ኖድ ጋር ለማገናኘት የሚጋሩት የወል ማገናኛ ማስመር ነው።

## <u>አባሪ ለ</u>

## <u>ለመሠረተ ልማት መጋራት ሊውሉ የሚችሉ የመሠረተልማት አይነቶች</u>

**1) ቋሚ መሠረተልማት (Passive Infrastructure)**

a. Rights-of-way
b. Antenna mast and tower structures
c. Dark fiber
d. Poles
e. Ducts
f. Trenches
g. Space in buildings
h. Shelters
i. Air conditioning
j. Sub-Loop (Wire or Cable)
k. Local Loop (Wire or Cable)
l. Electric power (public or private source)
m. Grounding/Earthing
n. In-House wiring.

**2) ገባሪ መሠረተልማት (Active Infrastructure)**

a. Radio Access Network (RAN) (MORAN or MOCN)
   i. BTS/Node
   ii. B/e-Node
   iii. antennae
   iv. feeder cable
   v. RAN
   vi. microwave radio equipment
   vii. BSC/RNC
b. In-Building Solutions (IBS)

viii. Distributed Antenna System (DAS),
ix. antennae,
x. feeder cable,
xi. splitters, and
xii. Combiners.

c. Optical/Wired Transmission Links.
d. Multiplexer (MUX)
e. Synchronous Digital Hierarchy (SDH)
f. Dense Wavelength Division Multiplexer (DWDM)